# ክብረ ድንግል

**በዚህ ንኡስ ርዕስ ውስጥ ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግል ክብርና አማላጅነት ተገልጾአል።**

## 1. የስምዋ ትርታሜ አባትና እናትዋ ስለምን ማርያም ብለው አወጡላት ቢሉ።

*እነሆ በዚህ ዓለም ከሚመገቡት ሁሉ ምግብ ላፍ የሚጥም ለልብ የሚወጥን ማር ነው።በገነትም በሕይወት የተዘጋጀ ጻድቃን ቅዱሳን ያም የሚባል ምግብ አላቸው። ሁለቱን ስናጋጥመው ማርያም የሚል እናገኛለን። ስለዚህ ከዚህ ሁሉ የበለጥሽ የከበርሽ ነሽ ሲሉ ማርያም ብለው አወጡላት ይላሉአባቶች።*

*ዳግመኛም ማርያም ማለት ጸጋ ወሀብት ማለት ነው። ለጊዜው ለእናት አባትዋ ሀብትና ጸጋ ሆና ተሰጥታለች። ፍጻሜው ግን ለምእመናት ሁሉ ጸጋና ሀብት ሆና ተሰጥታለች።*

*አንድም ማርያም ማለት መርህ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው። ይህስ እንዴት ነው ቢሉ እነሆ ዛራ በዚህ ዓለም ለእውር መሪ በትር እንዲሰጡት ሁሉ እርሷም በፍቅሯ በጣእመ ፍቅሯ የሰውን ሁሉ ኃጢአት ክፋት ፍቃ ከልጅዋ አስታርቃ ከገሃነመ እሳት አውጥታ መንግሥተ ሰማያት የምታገባ ስለሆነች መንግሥተ ሰማይ መርታ የምታገባ አቸት።*

*አንድም ማርያም ማለት ተላኪተ እግዚአብሔር ወስብእ ማለት ነው። እንዴት ነው ቢሉ መለኮት ከትስብእት ትስብእት ከመለኮት ተዋሕዶ በእመቤታችን በእግዝእትነ ማርያም መኅጸን አድሮ ነበርናስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የምትላላክ አሏት።*

<u>***መዝሙር*** 130 (131) ፥ 13 - 18</u>

**በዚህ ምእራፍ ላይ ጽዮን የሚላት በወርቁ እመቤታችንን ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ «ይህቺ ለዘለዓለም ማረፍያዬ ናት» ብሎ ለምድራዊነትዋ ጽዮን (ለምድሪቱ) አለመሆኑን ያረጋግጥልናል። ምክንያቱም «ሰማይና ምድር ያልፋሉ» ብሎ ራሱ ጌታ በማይታበል ቃሉ ተናግሯል። ስለሆነም ምድሪቱ የዘለዓለም ማረፊያው ልትሆን አትችልም። ለእመቤታችን ግን ይስማማል። «ይህቺ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት» ሲል ለዘለዓለም ወላዲተ አምላክ ስትባል የምትኖር ስለሆነ በተጨማሪም ደግሞ ከእሷ ለነሳው (የወሰደው) *ሥጋ* ለዘለዓለም መለኮትን ተዋሕዶ የሚኖር ስለሆነ «መርጫታለሁና አድሬባት እኖራለሁ» አለ።**

<u>**ትንቢተ ኢሳይያስ ፷ ፥** 4</u>

**- «የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሄር ከተማ (ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ማኅጸኑን ኣለም አድርጎ ተመስግኖበታልና ከተማ አለው) የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዬን ይሉሻል። ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ለእመቤታችን መስገድ እንዳለብን ያሳስበናል። ይህኮ ለማርያም ሳይሆን ለምድሪቾ እንድንሰግድ የምንገደድው እግዚአብሄር ሠላሣ ሦስት ዓመት በ*ሥጋ* ስለተመላለሰበት አይደለ ወይም ደግሞ መንፈሱ ስላደረባት አይደል?እነሆ ከምድሪቱ ጽዬን የምትበልጥ ልኡስ ባህርይን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅጸንዋ የተሸከመች**
**ታላቅዋ እመቤት አለች። ይህችውም የባህሪያችን መመኪያ የሆነችው ንጽህት ድንግል ማርያም ነች። እመቤታችን ከሰው ፍጥረት ሁሉ የተለየች ነች የምትባልበት ብዙ ምክንያት አለ። እግዚአብሔር በቅዱሳን ላይ ቢያድር በመንፈስ ነው። በእመቤታችን ግን ከ*ሥጋ*ዋ *ሥጋ* ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በአካል (በከዊን) ነው *ያደረው*። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስገነዝብ «የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም ዕብራ.** 2 ፥ 17 **ብሎአል። ሉቃስም በሐዋርያት *ሥራ*** 13፥22 - 23**» ከዳዊት ዘርእግዚአብሔር እንደተስፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም**

ኢየሱስን አመጣ» በማለት አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ መንሳቱን ያረጋግጥልናል። በዚ
ህም የተነሳ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ትባላለች።

እንግዲህ እመቤታችን ምን ያህል በአምላክ ዘንድ መመረጥዋንና መከበርዋን ልብ በሉ። ታዲያ ቅዱሳንለነበሩባት መ
ንፈሱ ላደረባት ምድር ስግደት የሚገባ ከሆነ ዘጠኝ ወር ለአምስት ቀን ማህጸንዋን ዓለም አድርጎ ለተመሰገነባት ለእ
መቤታችን በጸጋ የማይሰገድበት ምክንያቱ ምን ይሆን? ክህደት ካልሆነ በቀር ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም።

## <u>ሉቃስ ፩ ፥ 39 - 55</u>

ቅድስት ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን ድምጽ በሰማች ጊዜ በማሕጸንዋ ውስጥ ያለው ሕጻን በደስታ ዘለለ ይለናል። የጽ
ንስ እንቅስቃሴ ነው እንዳንል እራስዋ ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን ድምጽ ሰምቶ በደስታ መዝለሉን አረጋግጣልናለች።
ይህንንም ሐዋርያት «ሰገደ» ብለውታል። ለአምላክ ማኅደር ለእመቤታችን የጸጋ በማሕጸንዋ ውስጥ ላለው ለኢየሱ
ስ ክርስቶስ የአምልኮት ስግደት እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው እመቤታችንን ያከብራል እንደ ኤልሳቤትም
ያመሰግናል እንደ ቅዱስ ገብርኤል «ደስ ይበልሽጸጋ የሞላብሽ ሆይ» ይላል እንጂ እመቤታችንንአያቃልልም። አን
ዳንዶች እመቤታችንን የአዳም ኃጢአት አለባት ስለዚህም በደሙ ከተዋጁት ወገን ነች ይላሉ ነገር ግን እመቤታችን
ቅድስት ድንግል ማርያም የአዳም ኃጢአት የሌለባት በሥጋም በነፍስም ንጽሕት መሆንዋን መንፈስ ቅዱስ ከእናትዋ
ማሕጸንጀምሮ ያ በዘር የሚተላለፍ የመጀመሪያ ጥፋት ወደ እርሰዋ እንዳይተላለፍ ጠብቆአታል። ለዚህም ማስረጃ
የሚሆነን የቅዱስ ገብርኤል ምስክርነት ነው። «ጸጋ የሞላብሽ ሆይ» ማለቱ ከኃጢአት ከጥንትአብሶ (ከመጀመሪያው
በደል) ሁሉ የነጻች በሥጋም በነፍስም ንጽህት መሆንዋን የሚያመለክት ነው። ስለሞንም በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎ
ሞን 4፥7 ላይ «ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው፣ ነውርም የለብሽም» ብሎ እመቤታችን ነጥብ የምታክል እድፍ
ጉድፍ የሌለባት ንጽሕት መሆንዋን ይነግረናል።

በተጨማሪም እርስዋ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመጀመሪያ የመልአኩ ቀጥሎም የኤልሳቤጥ ሦስተኛ በ
ማኅጸን ያለውን የዮሐንስ ምስክርነት ይዛ አባትዋ ዳዊት በመዝ. 44፥16 ላይ ለልጅ ልጅ ስምሽን ያሳስባሉ ያለው ት
ንቢት እንደተፈጸመ አውቃ «ከእንግዲህ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመስግነኛል»በአንድ በመልአኩ ገብርኤልና በአንዲ
ት ኤልሳቤጥ ብቻ ተመስግኜ አልቀርም ብላ ተናገረች። በዚህም መሠረት እስከዛሬ ድረስ የክርስቶስ ወገኖች እመቤ
ታችንን ያከብራሉ ያመሰግናሉ።

መላእክት ሁሉ እመቤታችንን ያከብራሉ ያገናሉ ለእመቤታችንም ይሰግዳሉ። በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው መል
አኩ ቅዱስ ገብርኤል እንኳን ለዘካርያስ ልጁ እንደሚወልድ የምሥራች ቢነግረው ስለተጠራጠረ ቃሌን ስለአላመንክ
ብሎ ወዲያው ድዳ እንዲሆን አድርጎታል። ወደ እመቤታችን ሲቀርብ ግን ለየት አለ አቀራረብ ይዞ ነው የቀረበው
። የምሥራቹን ከመንገሩ በፊት ልብዋን በደስታ ለመሙላት ነውየሞከረው ደስ ያለሽ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበ
ልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ» ይህ የመልአኩ የምሥጋና ቃል
ከእዚህ ቀደም ለማንም ያልቀረበ በመሆኑ እመቤታችን ወዲያውኑ እሺ በጄ ብላ አልተቀበለችውም በዚህም ከእና
ትዋ ከሔዋን የተለየች መሆንዋ ይታወቃል መልአኩ ገብርኤል «ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው» ብላ በመለሰችለት
ወቅት አሁንም በትህትናና በአክብሮት «ማርያም አትፍሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነተን አግኝተሻልና» «ብሎ
ይዞት የመጣውን የምሥራች ቃል ነገራት። እመቤታችን ግን ብዙ ጥያቄ አቀረበችለት። መልአኩም እስከተቻለው
ድረስ መለሰላት በመጨረሻ ከባድ ጥያቄ በጠየቀችው ጊዜ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና» በሚለው አስ
ደናቂ መልስ የቃል ልውውጣቸውን ፈጸሙ።

እንግዲህ መልአኩ የዘካርያስን አንደበት በአንዲት የዘካርያስ የጥርጣሬ ንግግር ሲዘጋ።እመቤታችን ግንደግማ ደጋግ
ማ ላቀረበችለት ጥያቄ እንኳን እንደ ዘካርያስ ተቆጥቶ አንደበትዋን ሊዘጋ ቀርቶ መልሱን እንኳን ፍጹም ትህትና የ
ተሞላበት ነበር።

እንግዲህ ምን እንላለን በመላእክት ዘንድ እንጃን የከበረችውን እናት እኛ አናከብራትም ብንል ማን ይጎዳ ይሆን ጌ
ታ ለሳውል እንዲህ አለው። «የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል» አዎን?የዛሬ ጸረ ማርያሞችም እ
መቤታችንን ቢንቁ ለእነሱ ይብስባቸዋል እንጂ እሷንስ ኃያሉ ፈጣሪ አንድ ጊዜ አክብሯታልና ክብርዋን ሊነጥቅ የሚ
ቻል ሰው የለም።

**የዮሐንስ ራእይ 12፥1 … 7**

ክርስቲያን ወገኔ ሆይ የእመቤታችንን ክብር መጽሓፍ ቅዱስ እንዴት አድርጎ እንደሚገልጽ ልብ በል። ፀሓይን ተጎናጽፋ ጨረቃን ተጫምታ በራስዋም ላይ አሥራ ሁለት የክዋክብት አክሊል ሆኖላት። ለማንይሆን እንዲህ ዓይነት አገላለጽ ከዚህ በፊት የቀረበ ከቶ ለማንም ተጽፎ አላነበብንም። ይህ የተነገረው ለድንግል ማርያም አይደለም ብለው እንዳያብሉ ማስረጃው እዚያው ተጠቅሶላቸዋል።

«አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛውን» ማለት (በመለኮታዊ ሥልጣኑ ሕዝብን የሚገዛውን ልጅ የወለደች ከሴቶች ወገን ከቶ ማን ትሆን? ንጽሕት ስብሕት ቡርክት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምነች። መቼም ይጃን ቢክዱ እንጃን ሰው ሰይጣን ይታዘባቸዋል። በእመቤታችን የተነበረ መሆኑን ለማወቅ ሌላ ማስረጃ ካስፈለገ» ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጁቶላት ወደነበረው ሥፍራ ወደ በረሃ ሸሸች» የሚለውን መመልከት ነው። እመቤታችን ጌታንይዛ መሰደዱዋ በማቴ. 2፥13 - 18 ባለው ላይ ተጠቅሶአል።

እንግዲህ ዲያብሎስ በእመቤታችን ተቆጥቶ «የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር የሆኑትን ከእመቤታችን ከዘርዋ የቀሩትን ማለት በአማላጅነትዋ የሚተማመኑትን ሊዋጋ ሄዶ በባህር አሸዋ ላይ ቆመ ማለቶ በመናፍቃን ልብናና አንደበት ላይ ቆመ የእመቤታችንን ልጆች ሊቃወም።

## በመጽሐፍ ቅዱስ የእመቤታችን ምሳሌዎች በጥቂቱ

1. ገራሁተ ሠሉስ (የማክሰኞ ዕለት እርሻ) በዘፍጥረት 1፥9-13

   የመጀመሪያይቱ ምድር ገበሬ ሳይገርባት ፥ ዘር ሳይዘራባት ውኃም ሳያስፈልጋት በቃለ እግዚአብሔርብቻ ለፍጥረታት ምግብ የሚሆነውን ሁሉ ልታበቅል ችላለች። እመቤታችንም ያለ ወንድ ዘር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች። እርሱም በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ በዕጸ መስቀል ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ ክቡር ደሙን አፍስሶ እንኩ ሥጋዮን ብሎ ደሜን ጠጡ ብሎ ዘለዓለማዊ ምግብ ነፍስ ሆነልን።

2. የኖህ መርከብ ትባላለች ዘፍጥረት 7 ፥ 1 - 24

   የኖህ መርከብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ተመስላ ብትገለጽም አባቶች የእመቤታችንም ምሳሌ እንደሆነብ ይናገራሉ። እግዚአብሔር በኖህ ጊዜ የነበሩትን ሰዎች በኃጢአታችው ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው ሲያስብ ለኖህ መርከብ እንዲሠራ አዘዘው ኖህም መርከብ ሠርቶ ገባ። እግዚአብሔርም ምድርን ለአርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከላይ ከሰማይ ከታች ከምድር ውስጥ ውኃን በማዝነም በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች አንድ ሳይቀሩ ፈጃቸው። ኖህን ግን መርከብዋን ምክንያት አድርጎአዳነው ኖህ ሊድን የቻለው በሠራት መርከብ ጥንካሬና ብቃት አለመሆኑ ለማንኛውም ክርስቲያን ያልተሰወረ ነው። እግዚአብሔር ምክንያት ይሻልና መርከብዋን ምክንያት አድረጎ የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደሆነ የታወቀ ነው። እንዲህስ ባይሆን ኖሮ ያን መአተ እግዜአብሔር እንኳን የኖህ መርከብ ቀርቶ በአሁን ጊዜ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የተሠሩት ታላላቅ መርከቦችም ሊቋቋሙት አይችሉም። እንዲሁም ጌታ የአዳምን ልጆች ሊያድን ሲሻ እመቤታችንን ምክንያት አድርጎ ከእርስዋ ተወለደ ሁለተኛም በኖህ መርከብ በውሰጥዋ ያሉትን ሰዎች ከመከራ ሥጋ እንዳዳናቸው ሁሉ እመቤታንንም በአማላጁነትዋ የሚያምኑትን ሰዎች ከሞት ሥጋና ከሞተ ነፍስ ታድናቸዋለች። ከመርከብዋ ውጭ ያሉት በንፍር ውኃ እንዳጠፉ በእመቤታችን አማላጅነት የማያምኑትም በሥጋም በነፍስም ለዘለዓለም ይጠፋሉ።

3. በቀስት ደመና ትመሰላለች

   ከጥፋት ውሃ በኋላ እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን በንፍር ውኃ እንዳያጠፋት ለኖህ ቃል ኪዳን ገባለት። የቃል ኪዳኑ ምልክትም ቀስተ ደመና ነበር። እግዚአብሔርም ለኖህ የገባለትን ቃል ማጽናቱን ሊገልጽ ከአማናዊትዋ ቀስተ ደመና ከእመቤታችን ተወለደ። አስቀድሞ ነቢዩ በመንፈስ ቅዱስተቃኝቶ «እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር» ኢሳ. 1፥9። ሲል የእናት አማላጅ እውነተኛ መድህን እንደሆነልን ነገረን።

ስለሆነም እግዚአብሔር በኃጢአታችን ተቆጥቶ እንዳያጠፋን የባህሪያችን መመኪያ የምትሆን እመቤታችንን ከጎኑ አደረገልን።

4. **<u>በእጸ ሳቤቅ ትመሰላለች ዘፍጥረት</u>** <u>22 ፥ 9 - 13</u>
**ይስሓቅ የዚህ ዓለም በግ የጌታ ምሳሌ ነው። በጉ ለይስሐቅ ቤዛ ሆኖ እንደተሰዋ ጌታም የዓለም ቤዛ ሆኖ ተሰውቷል። በሌላ አገላለጽም ይስሓቅ የመለኮት በጉ የሥጋ ሰይፋ የሥልጣነ እግዚአብሔርስለቱ ለሕማም የሞት ምሳሌ ነው። እዚህ ላይ በጉ በእጸ ሳቤቅ ተይዞ ነበር። ይህም የእመቤታችንምሳሌ ነው። እርሷ ዓለምን ሁሉ በከበረ ደሙ የሚያድነው መድኃኔዓለምን ተፈትሆ በሌለበት ማህጸኑ በድንግልና አሥራ (ይዛ) ተሸክማ ለቤዛነቱ ጊዜ አድርሳዎለችና።**

5. **<u>ያእቆብ በፍናቴ ሎዛ ባያት መሰላል ትመሰላለች፣</u> ዘፍ** 28 ፥ 10 - 12
**እመቤታችን ያዕቆብ ሎዛ በተባለችው ሥፍራ በራእይ ያያትን መሰላል ትመሰላለች። መላእክት ይወጡባትን ይወርዱባት ነበረ። ጌታችን ከእመቤታችን ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ለተልእኮ አይወጡም አይወርዱም ነበር። ጌታ ከእመቤታችን ሰው ከሆነ በኋላ ግን ለተልእኮ የሚወጡ የሚወርዱ ሆነዋል። ሁለተኛም እርሷ ለቃል መውረድ ለሥጋ ዕርገት ምክንያት ሆናለችና አንድም አረገ መባሉ ከእርሷ የነሳውን ሥጋ በኩር አድርገው ነውና።**

**እንዲሁም ከምድር እስከ ሰማይ እግዚአብሔር መንበር የምትደርስ በላይዋም መላእክት ሲወጡባትእንደነበር እንዱሁ ደግሞ በቅድስት ድንግል እመቤታችን የአማላጅነት መሰላልነት የሰው ሁሉ ልመና ወደ ባህርይ አምላክ ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል። ያለ እመቤታችን አማላጅነት የማንም ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሊደርስ አይችልም።**

6. **<u>እፀ ጳጦስ ዘሲና ዘፀአት</u>** <u>3 ፥ 2 - 3</u>
**ሙሴ በሲና ያያት በእሳት የተከበበችው ቁጥቋጦ በእመቤታችን ትመስላለች። ሐመልማሉ ከነበልባሉ፣ ነበልባሉ ከሓመልማሉ ጋር አንዱ አንዱን ሳያጸፋ ተዋሕዶው መታየታቸው ጊዜያዊና ፍጻሜያዊምሳሌ አለው።**

**ለዚያን ጊዜ የነበረው ምሳሌ ሐመልማሉ የእስራኤል ነበልባሉ የሚደርሰባቸው መከራ ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያቃጥለው ማየቱ በመከራቸው አዝነው ንስሐ ገብተው ነጻ ለመውጣት የተዘጋጁ አለመሆናቸውንና በመከራ ውስጥ የሚጉዙ መሆኑን ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥላት ማየቱ መከራው የሚጸናባቸው ቢሆንም ጨርሶ የማያጠፉቸው መሆኑን ያመለክታል። ፍጻሜው ግን ነበልባል የመለኮት ሐመልማሉ የእመቤታችን ምሳሌ ነው። ቅዱስ ኤፍሬም እንያመሰለው ነበልባሉ በአካባቢው የነበሩትን ቁጥቋጦዎች ሲያቃጥል አንዲቱን ብቻ ያላቃጠለ መሆኑ መለኮትን በማህጸኑ ለመሸከም የተመረጠች ቅድስት ድንግል ማርያም መሆኑን አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን በነሳ ጊዜ የመለኮት ባሕርይ አላቃጠላትምና ባህርየ መለኮት ያልለወጣት መሆኑን የሚያመለከት ሲሆን እርሷን ሳያቃጥል ሌሎችን ቁጥቋጦዎች ማቃጠሉ ግን የመለኮትን ባሕርይ ለመሸከም ሌሎች የማይችሉ መሆናቸውንና የመለኮት ባህርይ የሚያቃጥላቸው መሆኑን ያስረዳል።**

7. **<u>የጌድዮን ፀምር መጽ. መሳ</u>** <u>6 ፥ 36 - 40</u>
**በወቅቱ ፀምር የእስራኤል ጠል የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ጠሉ በፀምሪ ላይ መውረዱ እግዚአብሔር እስራኤል በረድኤት የመረዳቱ በዳርና በዳር ባለው መሬት ላይ አለመውረዱ ረድኤተ እግዚአብሔር አሕዛብን የማይጠብቅና ከእነርሱ የራቀ መሆኑ ምሳሌ ነው። በሌላ በኩልም ፀምር የእስራኤል ጠል የመቅሰፍቱ ምሳሌ ነው። ጠሉ ከፀምሩ ላይ አለመውረዱ እስራኤል እግዚአብሔር ከመቅሰፍት ይጠብቃቸው የነበረ ለመሆኑ በዳር ባለው ምድር ላይ መውረዱ እግዚአብሔር አሕዛብን በየጊዜው በመቅሰፍት ያጠፋ የነበረ ለመሆኑ ምሳሌ ነው።**

**ፍጻሜው ፀምር የእመቤታችን ጠል የጌታ ምሳሌ ሲሆን ጠል በፀምሩ ላይ መውረዱ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ለነፍስዋ ነፍስ ለመንሳቱ በእርሷ የማደሩ ምሳሌ ነው። ጠል በጸምሩ ዳርና ዳር ባለው ምድር ላይ አለመውረዱ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርሰቶስበሌሎብ ሴቶች ያለማደሩ ምሳሌ ነው። ጠሉ በፀምሩ ላይ አለመውረዱ እመቤታችን ያለ ወንድ ዘር በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የመውለድዋ ሲሆን በዳርና በዳር ባለው ምድር ላይ መውረዱ ሌሎች ሴቶች በዘርእ ብእሲ በሩካቤ የመውለዳቸው ምሳሌ ነው። እንግ**

ዲህ እመቤታችን ከእንስተ ዓለም ተለይታ ያለወንድ ዘር ያለ ሩካቤ ጸንሳ በመውለድዋ በጌድዮን ፀምር ተመስላ ለች።

<u>ማጠቃለያ</u>

1. ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችን ስለእመቤታችን ያላት እምነት በአጭሩ ሲገለጽ «ጸጋ የተመላሽ እግዚአብሔር ካን ቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ ከሰዎች ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ የተባረክሽ ነሽና ደስ ይበ ልሽ» ሉቃስ 1፥28 በሚለው በመመሥረት እመቤታችን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ከእናትዎ ማሕጸን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ከአዳም ኃጢአት የጠበቃት ነች።

2. እናትና ድንግል ዘላለማዊት ድንግል በሐሳብ በሥራ ድንግል ነች።

3. በአማላጅነትዋ ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አገናኝታ በረከተ ሥጋና በ ረከተ ነፍስ ታስጠናለች።

4. «ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች» መዝሙር 44 ፥ 9 የሚለውን መሠረት በማድረግ ዛሬ በመንገሥተ ሰማያተ እን ዳለች ሞታ ያልቀረች በልጅዋ ኃይል የተነሳች መሆኑን ቤተክርስቲያን ታምናለች። መዝ. 131 (132) ፥8 መኃል የ መኃልይ ዘለሎሞን 2 ፥10 - 14።

ለንጹሐን ይልቅ ንጽሕት የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ሆይ ካንቺ ተጸንሶ የተወለደውን የባህርይ አምላክ ኢየሱስ ክ ርስቶስን ከደን በስሕተት ጎዳና እንዳንነጉድ ጠብቂን የልጅሽን ሥጋና ደምም ለመቀበል እንበቃ ዘንድ እያዘንሽ አማልጅን። የእኛ ሳንነጻ መቀበል ክቡር ልጅሽን ማዋረድ መናቅ እንዳይሆን እርሱን ልጅሽን በምትቀበይበት ጊ ዜ የተደረገን ያንቺን ንጽህና ስለ እኛ ፈንታ እንድታቀርቢልን እንለምናለን።

ከእንስተ ዓለም መርጦ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የሰጠን አምላክ ይክበር ይመስገን አሜን ! !

ዓምደ ሃይማኖት ከሚለው ብርሃኑ ጎበና በ1985 ካሳተሙት የተወሰደ።